## *ለወላጆች የተዘጋጁ ምን ዓይነት አገልግሎቶች ኣሉ?*

*ስለ ልጅዎ ትምርት መከታተል የሚመለከቱ ማንኛውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካልዎት፣ ለእርስዎ የተዘጋጁ አገልግሎቶችና እገዛዎች ኣሉ፡፡ ልብ ይበሉ፣ ትምህርት መከታተል ለሁሉም የሚመለከት ጉዳይ ነው፣ ስለዚህ እገዛ የሚፈልጉ ከሆነ ይጠይቁ፡፡*

የሚከተሉትን ማነጋገር ይችላሉ፡

- የልጅዎ ኣስተማሪ
- የትምርት ቤት ርእሰ-መምህር
- የትምርትቤት መመርያ አማካሪ
- የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጥ አስተማሪ
- የትምህርት ቤት ዲቪጅን የእገዛ አገልጎቶት ስራተኞች
- Manitoba Association of Parent Councils (MAPC)
- የማኒቶባ ትምህርት ሚኒስትር (Manitoba Education)
- ማኒቶባ ጤናማ ልጅ (Healthy Child Manitoba)
- www.manitobaparentzone.ca

Manitoba

***ዘወትር ክፍል ውስጥ መገኘት ለሁሉም ተማሪዎች አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በየቀኑ ትምርት የሚማሩ ተማሪዎች ከማንም ይልቅ በትምርት የተጠመዱ ናቸው፤ የማህበረሰቦቻቸው አካል መሆናቸው የሚገልጽ የላቀ ስሜት ያላቸው እና ይበልጥ የመመረቅ ዕድል ያላቸው ናቸው፡፡***

Manitoba Association of Parent Councils

**Manitoba Association of Parent Councils**

1005—401 York Avenue
Winnipeg MB R3C 0P8

ስልክ ቁ፡ 204-956-1770
ነጻ የስልክ መስመር፡ 877-290-4702
ፋክስ፡ 204-956-7780
ኢሜይል፡ info@mapc.mb.ca
Facebook: www.facebook.com/mapcmb
Twitter: www.twitter.com/mapcmb

Manitoba Association of Parent Councils

# ዘወትር በመደበኛነት ክፍል ውስጥ መገኘትን መደገፍ

*ወላጆች በማኒቶባ ትምርትቤቶች የሚሰጠው ትምርት ለመደገፍ ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች*



*የማኒቶባ ትምህርት ክፍል ከ2009 ጀምሮ በትምርት ቤቶች ውስጥ ትምርት የሚከታተሉ የተማሪዎች ቁጥር ከፍ እንዲል ለመርዳት በርካታ እንቅስቃሴዎች ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ **Manitoba Association of Parent Councils (MAPC)** በ2012 ላይ ለማኒቶባ ተማሪዎች ዘወትር በመደበኛነት ትምህርት የመከታተል አስፈላጊነትን በተመለከተ ለወላጆች ዕውቀት ለማስጨበጥ እንዲረዳ ከማኒቶባ ትምርት ክፍል ጋር ሽርክና መስርቷል፡፡*

# እያንዳንዱ ሰው በየቀኑ ትምርትቤት ውስጥ



# ያውቃሉን...?

- ማኒቶባ ውስጥ በየቀኑ ክፍል ውስጥ መገኘት የግድ እንጂ እንደ ፍላጎትዎ አይደለም፡፡
- ልጅዎ ዘወትር 10 ደቂቃ አርፍዶ ክፍል ውስጥ የሚገባ ከሆነ፣ የትምርት ዓመቱ ሲገባደድ ስድስት የትምርት ቀናት ያመልጠዋል ማለት እንደሆነ፡፡
- ልጅዎ በወር ውስጥ ሁለት የትምርት ቀናት ብቻ ካመለጠው፣ የትምርት ዓመቱ ሲገባደድ አንድ ወር የትምርት ግዜ ያመልጠዋል ማለት እንደሆነ፡፡
- ልጅዎ በእያንዳንዱ አመት 15 የትምርት ቀናት የሚያመልጠ ከሆነ፣ 12ኛ ክፍል በሚጨርስበት ግዜ አንድ ዓመት የትምርት ግዜ ያመልጠዋል ማለት እንደሆነ፡፡
- ዘወትር በትምህርት የሚገኙ ተማሪዎች ከማንም በበለጠ በመማር ላይ የተጠመዱ፣ የማህበረሰቦቻቸው ኣባል የመሆን የበለጠ ስሜት ያላቸው እና ይበልጥ የመመረቅ ዕድል ያላቸው ናቸው፡፡
- የሁለተኛ ደረጃ ትምርት ዲፕሎማ የሌላቸው ግለሰቦች ሁለተኛ ደረጃ ትምርት ካጠናቀቁ ተማሪዎች ሁለት እጥፍ ያኽል ስራ የማጣትና በአነስተኛ ደሞዝ የመቀጠር ዕድል ይኖራቸዋል፡፡

## እስከ 18 ዓመት ድረስ ትምህርት እንዲማሩ የሚያስገድድ ህግ

*የማኒቶባ ትምርት ክፍል መስከረም 2012 ላይ **Preparing Student for Success Act,** አስተዋወቀ፣ ይህም ተማሪዎች ትምርት እንዲማሩ የሚገደዱበት ዕድሜ ከ16 ዓመት ወደ 18 ዓመት ከፍ እንዲል ያደረገ ህግ ነው፡፡ የዚህ ህግ አላማ ማኒቶባ ከፍተኛ የተመራቂዎች ቁጥር እንዲኖራት እና ተማሪዎችም ስኬታማ እንዲሆኑ በርካታ ዕድሎች መሰጠታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡*

## ወላጆች ጥሩ የትምህርት ክትትል እንዲኖር ምን ማድረግ ይችላሉ?

- ለትምህርት ቤት እና ለትምርት ያለዎት ድጋፍ ለማሳየት ትምህርት ቤት ውስጥ በሚደረጉ ዝግጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ይሳተፉ
- ለጆችዎ ገና በልጅነታቸው ዘወትር በትምህርት ስለመገኘት ያነጋግሯቸው፡፡
- ከትምርትቤቱ ጋር በመደበኛነት በመወያየት ስጋቶችን ለማስወገድ በጋራ መስራት የሚቻሉባቸው ዘዴዎች ማፈላለግ
- ጫና ለማቅለል ልጅዎ ለቀጣዩ የትምርት ግዜ እንዲዘጋጅና እንዲያቅድ ይርዱት
- በሰፈራቹ ከሚኖሩ ሌሎች ቤተሰቦች ጋር ልጆች በጋራ ወደ ትምርት ቤት በእግር እንዲመላለሱ ለማድረግ ዕቅድ ያዘጋጁ
- በሚቻልበት ግዜ በትምርት መጀመርያ አከባቢ ላይ ቀጠረዎች ለማድረግ ያቅዱ
- በትምርት ዓመት መሃል የዕረፍትና የመዝናኛ ግዜ እንዲኖርዎ ዕቅድ ያውጡ
- የተማሪዎች ማመላለሻ ኣውቶቡስ ስለ ማስጀመር ከትምርት ቤትዎ ጋር ይነጋገሩ

**ተግባሮቻችሁ ከቃላቶቻችሁ በላይ ይናገራሉ!**

**በሰዓትዎ በመገኘት ለዘወትር ክፍል ውስጥ**

**መገኘት እና ለትምህርት ያለዎት ክብር ያስመስክሩ፡፡**

## ትምርት ቤቶች ጥሩ የትምርት ክትትል ለመደገፍ ምን ማድረግ ይችላሉ?

- እያንዳንዱ ልጅ ችግር በሚያጋጥመው ግዜ ሊያነጋግረው የሚችል በትምህርት ቤቱ ውስጥ

  ታማኝ የሆነ አዋቂ ሰው መኖሩን ለማረጋገጥ ይስሩ
- ልዩ በዓላትን እና በትምርት ቤቱ ውስጥ የወላጆች ተሳትፎን በማስመልከት ከቤተሰቦች ጋር በመደበኛነት ይነጋገሩ
- ተማሪዎችና ቤተሰቦች በትምርት ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ ክብር ማግኘታቸውን እንዲያውቁ መልካም አቀባበል ያድርጉ